# **<u>የኢትዮጵያንና የኤርትራን ያልተቋጨ እሰጥ አገባን ለመስበር፣</u>**

ከገራገር ዘበርጋ፣(26/01/2017)

***<u>መግቢያ፣</u>***

በኢትዮጵያና በኤርትራ በኩል ያላችሁ አንባቢዎች የሁለቱም አገራት የወቅቱ <<ሰላም የለሽ፣ ጦርነት የለሽ>> አቋም ምን ያህል የሁለቱንም ሕዝቦች ኑሮና ሕይወትን በከፋ ደረጃ እየጎዳ እንደሚገኝ የምትገነዘቡት ይመስለኛል። በርግጥ የጉዳቱ መጠን ካንዱ አገር ወደ ሌላው ሊለያይ እንደሚችል የተለያዩ ማስረጃዎችን እየዘረዘሩ ማቅረብና ማረጋገጥ የሚቻል ቢሆንም ያሁኑ መነጋገሪያ ርእስ ግን በዚህ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ስላልሆነ የሕዝቦቹ ቀጣይ ጉዳት መኖሩን ብቻ በመግለጽ ላልፈው እፈልጋለሁ።

ሁለቱም አገራት ከባድመ ጦርነት ወዲህ በጠላትነት ዓይን እየተያዩ እንደቀጠሉና ይህም ክስተት ከ1990 ዓ.ም የባድመ ወረራ ወዲህ 19ኛ ዓመቱን ሊደፍን እየተቃረበ እንደሚገኝ ግልጽ ነው። ጦርነቱ በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ቢደመደምም የድንበር ኮሚሽኑ የኃላ ኃላ በሰጠው ውሳኔና ውሳኔውንም ለመተግበር በተከተለው ውዝግብ ምክንያት ሁለቱም አገራት ዓይን ለዓይን ላለመተያየት በተከተሉት የተሳሳተ መንገድና ምናልባትም የዲፕሎማሲ ግድፈት ሊባል በሚችል አካሄድ በድንበር አካባቢ በሁለቱም ወገኖች በኩል ከፍተኛ ጦር በማስፈር የ<<ሰላም የለሽ፣ ጦርነት የለሽ>> እውነታን ፈጥረው የውጥረት ሕይወት እንዲቀጥል ተደርጓል። ለዚሁም ይመስላል በሁለቱም ድንበር አካባቢዎች ማለትም በኢትዮጵያ በኩል በቡሬ፣ በኤሊዳር፣ በባዳ፣ በዛላምበሳ፣ በእገላ፣ በአሕስኣ፣ በራማና በባድመ ወዘተ…፤ በኤርትራ በኩል ደግሞ በአሰብ፣ በማይቲ፣ በበይሉል፣ በምራራ፣ በጾሮና፣ በማይምነ፣ በምሽኳ፣ በሽምቦቆና በኦምሓጀር ወዘተ… አካባቢዎች የረባ ልማት እንቅስቃሴ ለማካሄድ አለመቻሉን ስንመለከትና በዚህ አካባቢ የሚኖረው ሕዝብም የቆቅ ሕይወት ማለትም በስጋትና በፍራቻ መኖር መቀጠሉን ስንመለከት ጉዳቱ እጅግ አሳሳቢ ያደርጓል። ታዲያ የሚገርመው ጉዳይ የዚህ አካባቢ ሕዝብ በትግራይ ድንበር ያለውም ይሁን በኤርትራ ድንበር የሚገኘው ሕዝብ ከጦርነቱ በፊትና ከዚያም ቀደም ብሎም በማሕበራዊ ሕይወቱ በጣም የሚቀራረብና ብሎም በደስታና በሐዘን ጊዜም የማይለያይ ሕዝብ ስለነበረ ከውጥረቱ መፈጠር በኃላም ሳይቀር አንዳንዴ በምልክት፣ በምስጢርና በጨለማ መገናኘቱ አልቀረም። ከኢትዮጵያ በኩል ዜጎቹ በኤርትራ መንግስት ጠባቂዎችና የደህንነት አባላት እጅ እንዳይወድቁ በመስጋት ዜጎቹን ማስጠንቀቁን የቀጠለበት ቢሆንም ከኤርትራ በኩል ግን እንኳንና በምስጢር ዘመዶቻቸውን ጠይቀው የሚመጡትን ይቅርና ድንበር የመሻገር እቅድ ወይም ሐሳብ ሊኖራቸው ይችላል ተብለው የሚጠረጠሩትን ሲያስርን ሲያንገላታ ምናልባትም ሲገድል ከርሟል።

## ሀ. <u>የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ቀጣይነት፣</u>

የድንበር ውጥረቱ ከተከሰተ ወዲህ በድንበር አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ በተለያየ መንገድ ሲገናኝ ቆይቷል። ለዚሁም እንደአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉትን ክስተቶች ልጥቀስ።

1. በዛላምበሳ አካባቢ ሕዝቡ የሚኖርበት ድንበር የሚለያየው በሚታረስ ማሳ ደረት ነው። ስለሆነም የሁለቱም አገራት ገበሬዎች ማሳቸውን ማረስ ካለባቸው እስከ ደረቱ ጥግ ነው የሚያርሱት። በመሆኑም ፊት ለፊት መገናኘታቸው ስለማይቀር የልባቸውን ከማውራት የሚያግዳቸው ነገር የለም። በዚሁ ድንበር አካባቢ ሰው ሲሞትና ሐዘን ሲያጋጥም መርዶ ነጋሪዎች እየዞሩና እየጮሁ ማን እንደሞተና ቀብሩም የት እንደሚፈጸም በግልጽ እየሰሙት

ስለሆነ የሚከናወነው ምንም እንኳን ሕዝቡ ድንበሩን ወይም የማሳ ደረቱን አልፎ ለመሄድ ያለው የፀጥታ ሁኔታ ባይፈቅድለትና በቀብሩ ላይ ለመገኘት ባይችልም ሐዘኑን በለቅሶና በማስተዛዘን ማከናወኑ ግን ደረቱን (ድንበሩን) ሳይሻገርም የሐዘኑን ሂደት ከማከናወን የሚያግደው የለም። ሐዘናቸው ሲገልጹም ያንዱ አገር ሕዝቦች በኪሎሜትር ርቀት እንደሚተያዩ ሆነው በመደዳ ይቆሙና የሌላው አገር ሕዝቦች ደግሞ በወዲያው ድንበር እንዲሁ በኪሎሜትር ርቀት በቅጡ እንደሚተያዩ ሆነው በመደዳ ይቆማሉ። ከዚያ በኃላም አስተዛዛኝ ሕዝቡ ጎንበስ ብሎ <<ጽናቱን ያስጣችሁ!>> የሚል መልእክት ከማዶው ላለው ለሐዘንተኛው ሕዝብ ያስተላልፋል። ሐዘንተኛው ሕዝብ ደግሞ <<በኛ የደረሰ አይድረስባችሁ!>> በሚልና ጎንበስ በማለት የመልስ መልእክት ይሰጡዋቿል።(1) በዚሁ ሂደትም የሐዘን ስነ ስርዓቱ በሁለቱም ወገኖች ይከናወናል። ይህንን የሕዝብ የተለመደ ባህላዊ ተግባር ምናልባት ጦር የሰፈረበትና <<አትለፉ፣ ከፊታችን አትቁሙ>> የሚል ቁጥጥር ከሌለው በስተቀር በየትኛውም አስተዳደራዊና የፀጥታ ቁጥጥር ሊታገድ የሚችል ክስተት አይደለም።

2. የድንበር ገበሬዎችና እረኞች በሚያውቁዋቸው የድንበር በርካታ መተላለፊዎችም የተለያዩ የእህልና የቤት ፍጆታ ለማዶዎቹ ዘመዶች በድብቅ ማስተላላፍም የተለመደ ክስተት እንደሆነ ይነገራል።(2)
3. ዘመዶችን አሻግሮ ወደ ኢትዮጵያ እንዲያልፉ የማድረግ ተግባርም ምንም እንኳን ለአደጋ የሚያጋልጥ ቢሆንም የመጣው ይምጣ ተብሎ የሚወሰድ የተለመደ ያንዳንድ የድንበር ነዋሪዎች ተግባር እንደሆነ ያደባባይ ምስጢር ነው። ለዚሁም ይመስላል ድንበር ተሻግሮ ወደ ኢትዮጵያ እየገረፈ ያለው ኤርትራዊ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዶ ባሁኑ ጊዜ በስደተኛ ማእከላት ብቻ ወደ 170.000 የሚጠጋ ስደተኛ ተጠልሎ ይገኛል። ይህ እንግዲህ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር የወጣውን፣ በኢትዮጵያ ካሉት ዘመዶቹ ጋር ተጠልሎ ቋሚ ሕይወት እየመራ የሚገኘውን፣ በዩኒቨርሲቲዎች፣ በሁለተኛና አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች እየተማረ የሚገኘውን፣ ከውጭ ጥሪ ይመጣልናል እያሉ ባዲስ አበባ ኮንደሚንየም ቤቶች በትንሽ ኪራይ በብዛት ሆነው ተከራይተው እየኖሩ የሚገኙትን በርካታ ወጣቶችን ወዘተ… ሳይጨምር ነው።(3)
4. በዚህ ዓመት ማለትም በ2009 ዓ.ም የአክሱም ጽዮን በዓልም ከድንበር አካባቢ ተደብቀው ገብተው ኢትዮጵያዊያንም ረድተዋቸውና መርተዋቸው በድብቅም የሚያውቅ አካል እንቅስቃሲያቸውን እያወቀውም አክሱም ድረስ መጥተው ለፈጣሪያቸው ጸሎት አድርሰው የተመለሱ ኤርትራዊያን እንዳሉም በቅርብ ጊዜ ከሁነኛ ምንጭ ያገኘሁት መረጃ አረጋግጦልኛል።(4)
5. ከላይ የተጠቀሰው ሂደት የድንበር ሕዝቡ የዘወትር ተግባር ሲሆን ከጾረና ጀምሮ እስከ ባድመ አካባቢ በመረብ ወንዝ የሚካለለው ሕዝብ ቢሆንም ማዶ ለማዶ ሲተያይ ስለሚውልና በወንዙ ሲጠቀምም የሚገናኝበት ሁኔታ ስለሚኖር የተለያዩ የጋራ መስተዋህዶች ቢከሰቱ ሊያስደንቅ የሚችል አይሆንም።

ለ. <u><<ሰላም የለሽ፣ ጦርነት የለሽ!>> ፖሊሲ፣</u>

የሁለቱም አገራት መንግስታት ከድንበር ግጭቱ ወዲህ የሚከተሉት ፖሊሲ ሌላ ምንም ዓይነት ግንኙነት ሳይኖር <<አትንካኝ፣ አልነካህም!>> ወይም <<አትምጣብኝ፣ አልመጣብህም!>> ወይም <<ጦርነት ካልከፈትክብኝ እኔም አልነካህም!>> ወዘተ… የሚመስልና ድንበሩ ግን ለ<<ሰላም የለሽ፣ ጦርነት የለሽ!>> ሁኔታ ተጋልጦ እንደሚገኝና ባንጻሩ ግን

ከሁለቱም ወገኖች ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጦር በየድንበሮቻቸው አካባቢ ሰፍሮ እንደሚገኝ ያደባባይ ምስጢር ነው። ታዲያ ይህ ሁኔታ እስከመቼ የሚቀጥል ነው? ብለን የጠየቅን እንደሆነ ማንም መልስ አለኝ ብሎ የሚቀርብ አካል እንደሌለና ሁለቱም መንግስታትም ጭምር ይህ የ<<ሰላም የለሽ፣ ጦርነት የለሽ!>> ሁኔታና ክስተት የመቋጫው ጊዜ መቼ እንደሆነ እንደማያውቁትና እንዲያውም ክስተቱ የመቋጫ ጊዜ ይኑረው ወይም አይኑረው ብዙም የተጨነቁበት እንደማይመስሉ ከሚያደርጉት እንቅስቃሴና ካሉት ሁኔታዎች መገንዘብ ይቻላል። ለምን? እስከመቼስ?

1. በኤርትራ መንግስት በኩል ያለው ፖሊሲ የመረመርን እንደሆነ <<በድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ምክንያት ለኔ የተወሰነልኝን መሬት ኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ ባለመፈለጓ ምክንያት አሁንም መሬቴ ወይም ግዛቴ በኢትዮጵያ ተወሮና ተይዞብኝ ይገኛል፣ ለዚሁ ሁነኛ አብነትም ባድመ ለኔ ተወስኖልኝ ሲያበቃ ኢትዮጵያ በቁጥጥሯ ስር አድርጋ ስታስተዳድረው ቀጥላለች። ይህ በውሳኔ ያገኘሁት ግዛቴ ኢትዮጵያ ወዳም ይሁን በኃያላኑ መንግስታት ተገድዳ እንድትሰጠኝ ካልተደረገ ከኢትዮጵያ ጋር እርቅ ብሎ ነገር የለም>> የሚል አቋም በመያዝ ሲቀሳቀስ ከርሟል።
2. በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ያለው ፖሊሲ ደግሞ ስንመረምር <<በድንበር ኮሚሽን ውሳኔ መሰረት የተላለፈው ውሳኔ ለመተግበር በባድመ ብቻ ሳናተኩር በርካታ የኤርትራ መሬት ለኢትዮጵያ ይሁን የተባለ አለ፣ በርካታ የኢትዮጵያ መሬትም ለኤርትራ ይሁን የተባለ አለ፣ ውሳኔው ሁለታችንም ቁጭ ብለን ካልተነጋገርንበት በስተቀር ጉዳዩ ካንዱ አገር ወደ ሌላው መሬት በማስተላለፍ ብቻ የሚፈታ አይደለም፣ መሬቱ ሲተላለፍ በቦታው ሕዝብም ስላለ ሕዝቡስ ምን ይሁን ሳንል በደምሳሳው አንተ ይህን ውሰድ! አንተም ይህን ውሰድ! በሚል አካሄድ ዘላቂ መፍትሔ ሊሰጠው አይችልም፣ ስለዚህ የሁለቱም አገር የድንበር ሕዝብ ለክፍለ ዘመናት አብሮ የኖረና የተሳሰረ በመሆኑ እንዲሁ የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ ምን አለ? በሚል ብቻ ሊፈታና ሊስተካከል የሚችል ስላልሆነ ቁጭ ብለን ተነጋግረን እንፍታው>> የሚል አቋም እንዳለው በተደጋጋሚ ይነገራል።
3. የኤርትራ መንግስት ኢትዮጵያ ያቀረበችውን የእንነጋገር ሐሳብ <<በፍጹም አልቀበልም! መሬቱ ይሰጠኝና ከዚያ በኃላ እንነጋገራለን>> የሚለውን አቋሙን አጥብቆ በመያዝ የቀጠለ ሲሆን የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ <<ቁጭ ብለን ካልተነጋገርን አሳልፌ የምሰጠው መሬት የለኝም>> የሚለውን አቋሙን አጠናክሮ ይዟል።
4. ሁለቱም መንግስታት ከጦርነቱ ማግስትና ከድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ በኃላ ከላይ የተገለጸውን ተጻራሪ አቋም በመያዝና በጠላትነት መቀጠላቸው እንዳለ ሆኖ ከዚሁ ጋር በተያያዘም አንዱ መንግስት የሌላውን መንግስት ተቃዋሚ በማጠለልና ድጋፍ በማድረግ ተቃራኒውን መንግስት ወይም አገር የሚጎዳበትን ወታደራዊና ኢንተሊጀንሳዊ ተግባርን ሲያካሂዱ ከርሟል። ምንም እንኳን በኢትዮጵያ የተጠለሉት የኤርትራ መንግስት ተቃዋሚዎች ተጠናክረው መውጣት ባይችሉና አስጊ ኃይል ሆነው ለመገኘት ባይችሉም በየጊዜው ስብሰባዎችንና ጉባኤዎችን በማድረግ ተቃዋሚነታቸውን ለማሰማት ሲንቀሳቀሱ ይታያል። በኤርትራ መንግስት በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ መንግስትን የሚቃወሙ ወገኖችን በማደራጀት፣ በማሰልጠንና በማስታጠቅ ከዚያም አልፎ አንዳንዶቹን ወደ አገሪቱ ሰርገው እንዲገቡና ጉዳት እንዲያደርሱ በማድረግ ሲንቀሳቀስ ከርሟል፣ አሁንም እየቀጠለበት ይገኛል። እንግዲህ ጠላትነት ጥሩ ጎን ሊኖረው አይችልምና ሁለቱም መንግስታት የጥላቻቸውን ደረጃ ከጫፍ እንዲደርስ አድርገውት ይገኛል። በመሆኑም የጠላትነት ደረጃው መውጫ ቀዳዳ የሌለው እስኪመስል ድረስ ሁለቱንም አገራት ከውጥረት ላይ አስገብቶዋቸው ይታያል። ሁለቱም መንግስታት አንዱ መንግስት በሆነ መንገድ

እንዲወድቅላቸው እስከመመኘት በሚመስል አካሄድ መውጫው መንገድን አጥተው እየባዘኑ ያሉ ይመስላል።

ሐ. <u>ሰርጎ ገቦችን ማሰማራትና ተመጣጣኝ የአጸፋ እርምጃ፡</u>

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ላለፉት አስራ አምስት ዓመታት ሁለቱም መንግስታት የያዙትና ያዋጣናል ብለው ተግባራዊ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ አለ።

1. በኤርትራ በኩል የሶማሌ አቦ፣ የኦነግ፣ የግንቦት ሰባት፣ የአርበኞች ግንባር፣ ወዘተ… ጀሌዎችን በማሰልጠንና በማስታጠቅ ከተቻለም ከታሪካዊ የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር በማበር ሰርጎ ገቦችን ወደ ኢትዮጵያ በማስገባትና የልማት ተቋማትን ለማውደም፣ አህጉራዊ ስብሰባዎችን ለማደናቀፍ ወዘተ… ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደረገ ሲሆን ከዚሁ በተጨማሪም የሶማሊያ ጦረኞችንና አሸባሪዎችን እስከመደገፍ፣ ማጥለል፣ ማሰልጠን፣ ማስታጠቅና ማሰማራት የደረሰ ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊና ኢንተሊጀንሳዊ ወዘተ… ተግባራትን በመፈጸም የኢትዮጵያን ጥቅም ለመጉዳት ያልተቋረጠ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ከርሟል። በዚህም የኤርትራ መንግስት ተግባር አብዛኛው የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ የፀጥታ ሓይሎችና በሕዝቡ የነቃ እንቅስቃሴ በእንጭጩ የከሸፉ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ጥቃቶች ግን ጉዳትን አድርሰው ያለፉበት ሁኔታም ይኖራል።
2. የኢትዮጵያ መንግስት የተከተለው ፖሊሲ ደግሞ <<የኤርትራ መንግስት አንዳች ጥቃት በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ ያደረሰ እንደሆነ ተመጣጣኝ ያጸፋ እርምጃን በመውሰድ ማስታገስ>> የሚል አቋም ይዞ ሲንቀሳቀስ ከርሟል። የኤርትራ መንግስት ሰርጎ ገቦችን በመላክ ወይም ራሱ ባሰማራው ኃይል አንድ ጉዳት ሲያደርስ የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ ተመጣጣኝ ያጸፋ እርምጃ ወስጃለሁ በማለት ሲከላከል እንደቆየና አሁንም ይህንኑ አቋሙን አጠናክሮ እየቀጠለበት ይገኛል። በመሰረቱ የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን <<ተመጣጣኝ ያጸፋ እርምጃ>> የሚለውን አቋም ባይዝና ጦርነትን የሚጋብዝ የኃይል እርምጃ ለመውሰድ ቢጋበዝ ኖሮ አሁን እያቀላጠፈው የሚገኘውን ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት በጣም ይቸገር እንደነበር እሙን ነው። ለምን ቢባል በሁለቱም አገራት ድንበር አካባቢ ጦርነት እንደተቀሰቀሰ በሚመስል ሁኔታ የሆነ እንቅስቃሴ ቢደረግ ኖሮ ኢትዮጵያ ከውጭ የምታገኘውን የውጭ እርዳታና ብድር፣ የውጭ ኢንቨስተሮች የሚያፈሱትን መዋእለ ንዋይ፣ ባጠቃላይም ባገሪቱ የሚካሄደውን የልማት እንቅስቃሴ ክፉኛ የሚጎዳበት ሁኔታ ይፈጠር እንደነበር ስለሚገመትና ስለሚታወቅ የኢትዮጵያ መንግስት <<ሰላም የለሽ፣ ጦርነት የለሽ!>> ፖሊሲው ጠቅሞኛል እንጂ አልጎዳኝም የሚል ይመስላል። ለነገሩ የጦርነት ሁኔታ በድንበር ማንዣበቡ ቢታወቅ ወይም ቢሰማ ኖሮ ማን ደፍሮ ገንዘቡን በኢትዮጵያ ምድር ላይ ያፈሳል? በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ በባድመና በሌሎችም ድንበር አካባቢዎች ተቀስቅሶ በነበረው ጦርነት ምክንያት የዓለም የገንዘብ ተቋማት፣ የልማት አጋር አገራትና መንግስታት እንዲሁም ኢንቨስተሮች ምን ያህል ከኢትዮጵያ መንግስት የልማት እንቅስቃሴ ተቆጥበውና እጃቸውን ሰብስበው እንደነበረ ከኢትዮጵያ መንግስት የበለጠ የሚያውቀውና ጉዳቱን የተሰማው ኃይል ያለ አይመስለኝም። ስለሆነም ምንም እንኳን በድንበር አካባቢ ሊኖር ይችል የነበረው ልማት እጅጉን የጎዳው ቢሆንም በሌላው የኢትዮጵያ አካባቢ ግን ልማቱ መፋጠኑ በግልጽ ይታያል።
3. በኤርትራ በኩል ያለው የልማት እንቅስቃሴ ውሱን እንደመሆኑና በመንግስት ራሱ የሚከናወንና አንዳንዴም ከውጭ ባለሀብቶች ጋር መንግስት በሽርክና የሚያካሂደው የልማት እንቅስቃሴ በመሆኑ የ<<ሰላም የለሽ፣ ጦርነት የለሽ!>> ሁኔታው የዓለም የገንዘብ ድርጅቶች እርዳታና ብድር እንዳይሰጡ፣ የውጭ ኢንቨስተሮች ገንዘባቸውን ይዘው እንዳይገቡ፣ ወዘተ…

እንቅፋት ሊፈጥር ይችላል የሚባልበት ክስተት ሊፈጥር አይችልም። ምክንያቱም የመንግስቱ ፖሊሲ እነዚህን ኃይላት የሚያሳትፍ ስላልሆነ። ነገር ግን አገሪቱ ውስጣዊ ሰላም ቢኖራትና ከኢትዮጵያ ጋር ያላት ግንኙነት ሰላማዊ ቢሆን ኖሮ እነዚህ ገንዘብ ያላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ባለሃብቶች በኢትዮጵያ እንደሚያደርጉት ሁሉ በኤርትራም ገንዘባቸውን ለማፍሰስ የማይዘጋጁበት ሁኔታ አይኖርም ነበር ለማለት አይቻልም።

4. ይህ የ<<ሰላም የለሽ፡ ጦርነት የለሽ!>> ሁኔታ እስከ መቼ መቀጠል አለበት? ለሚለው ጥያቄ በሁለቱም አገራት በኩል ግልጽ የሆነ ራእይ ወይም አመለካከት አለ ለማለት አይቻልም። ሁለቱም መንግስታት ያንዱ መንግስት በሆነ ተዓምር እንዲወገድለት ወይም እንዲወድቅለት የሚጠባበቅ ይመስላል። ለነገሩ የኤርትራ መንግስት የሚያስበው <<የኢትዮጵያ መንግስት በዘር በተመሰረተ ፌዴራሊዝም የተዋቀረ ስለሆነ ጊዜ ይፈጃል እንጂ አንድ ቀን ስርዓቱ ራሱን በራሱ ተባልቶ ይፈርሳል>> የሚል የተሳሳተ አቋም እንደሚያራምድ ይታወቃል። ስለሆነም የፈጣሪም ኃይል ተጨምሮበት ይህ ውድቀት አንድ ቀን እንዲከሰትለት ይጠባበቃል፡ አሊያም ይህንኑ ውድቀት ሊያግዝ ይችላል የሚለውን የታጠቀን የሰርጎ ገብ ኃይል በማደራጀትና ወደ ኢትዮጵያ አሰርጎ በማስገባት የኢትዮጵያን መንግስት ለመጉዳት ይሞክራል። ከተቻለም ከሌሎች የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር በማበር የብሄር ብሄረሰብ ክፍተቶችንና የማንነት ጥያቄዎችን አጉልቶ በማውጣት ሕዝቡን ለማነሳሳት ገንዘብ ይረጫል፡ ያስተላልፋል፡ ኃይል ያደራጃል። ነገር ግን የኤርትራ መንግስት በዚህ ዓይነቱ የተሳሳተ ስልት ይወድቃል ወይም ይበታተናል ብሎ የሚያስበው የኢትዮጵያ መንግስት እንዲሁ ሊወድቅ የሚችል እንዳልሆነ የተገነዘበ አይመስልም። ስለሆነም አስተሳሰቡ ራሱ ከእውነታ የራቀና ግብዝ ስለሆነ ይህንን መሰረት አድርጎ የሚጠብቀው ውጤት አይሳካምና ሌላ የሚያዋጣውና ዘላቂነት ያለው አቋም ወይም ፖሊሲ ነድፎ ቢንቀሳቀስ ይበጀዋል እላለሁ።

5. በሌላም በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ መንግስት የ<<ሰላም የለሽ፡ ጦርነት የለሽ!>> ሁኔታው ወይም ክስተቱ እስካሁን ድረስ ከላይ በተገለጸው መለኪያ ለኢኮኖሚው ልማት እንደጠቀመው የሚታወቅ ቢሆንም ካሁን በኋላ ግን ይህ ዓይነቱ መቋጫ የለሽ ሁኔታ እንዲለወጥ ሌላ መንገድ ወይም ስልት መቀየስ ይኖርበታል። በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ መንግስት እንደሚገምተው የኤርትራን መንግስት በውስጥ ችግሩ ተገፋፍቶና ራሱን በራሱ ተጥመልምሎ ይወድቃል ብሎ የሚያስብ ከሆነም የተሳሳተ መንገድ ይመስለኛል። የኤርትራ መንግስት ከልምድ እንደታየው በመፈንቅለ መንግስት ይሁን በሌላ መንገድ በቀላሉ የሚወድቅ አይመስልም። የመከላከያና የፀጥታውን ኃይል አንዱ ክፍል በመንግስቱ ላይ ወይም በሌላው ክፍል ላይ ምንም ዓይነት ተቃውሞ እንዳያስነሳ ተደርጎ የተዋቀረ በመሆኑና ተቃውሞ ቢነሳም በቀላሉ በሌሎች ክፍሎች ለመደፍጠጥ በሚቻልበት ሁኔታ የተደራጀ በመሆኑ የኤርትራ መንግስት በዚህ ዓይነቱ ስልት በቀላሉ እንደማይወድቅ መታወቅ ያለበት ይመስለኛል። አንዳንድ ወገኖች አቶ ኢሳያስ ቢወገዱ ስርዓቱ ለውጥ ሊያደርግ እንደሚችልም የሚገምቱ አሉ። ይህ አስተሳሰብም ስህተት ይመስለኛል። አቶ ኢሳያስ በሆነ ሁኔታ ከስልጣን ቢርቁ ወይም ቢወገዱ ከመቅጽበት በኤርትራ ውስጥ ለውጥ ይመጣል ብሎ መገመት የዋህነት ብሎም ግብዝነት ነው። አቶ ኢሳያስ ቢገለሉ በርካታ ተተኪ ኢሳያሶች ይገኛሉ። በኤርትራ ለተፈጸመው ወይም ለደረሰው ጉዳት ወይም ክፍተት አቶ ኢሳያስ ብቻ ናቸው ተጠያቂ ብሎ መደምደም ስህተት ይመስለኛል። አቶ ኢሳያስ ቁንጮው ቢሆኑም ከስር ተሰልፈውና ተደራጅተው ስርዓቱን የሚያንቀሳቅሱ በርካታ ኢሳያሶች እንዳሉ እውነታውን አለመቀበል ስህተት ይመስለኛል። አቶ ኢሳያስን ሊተኩ የሚችሉ በርካታ ሰዎች እንዳሉና የስርዓቱ መቀጠልም ከሕልውናቸው ጋር በማያያዝ የሚንቀሳቀሱ በርካታ መሪዎችና ተከታዮች እንዳሉ አለመገንዘብ የዋህነት ይመስለኛል። ሰሜን ኮርያ ለሦስት ትውልድ ባንድ ቤተሰብ እየተመራች እንደምትገኝና ከብዙ

አቅጣጫ ተቃውሞ ቢበዛባትም ስርዓቱን ለመለወጥ በጣም አዳጋች ሆኖ እንደቀጠለ ማየቱ ራሱ ለኤርትራ ሁኔታም ትምህርት ሊሆን ይገባል። የዓለም ህብረተሰብ ከሰሜን ኮርያ ጋር ያለውን ግንኙነት ለመለወጥ ወይም ለማስተካከል አለመቻሉን ስንመለከት ደግሞ ተጠያቂነቱ የሰሜን ኮርያ ብቻ ሳይሆን የዓለም ህብረተሰብ ድክመት መሆኑንም ለማየት ቆም ብሎ ማሰላሰልን ሳይጠይቅ አይቀርም። አቶ ኢሳያስም ዋዘኛ ሰው ናቸው ብሎ መገመት የማይቻለው የአየር ኃይላቸውን ምክትል አዛዥነት ለልጃቸው እንዲሆን ማድረጋቸውን ስንሰማ ለምን እያዘጋጁት ይሆን? የሚል ጥያቄን እንድናነሳ ከሚገፋፋን በስተቀር <<እርሳቸው በቅርብ ጊዜ ስልጣናቸውን ይለቃሉ ወይም ቢገለሉ ስርዓቱ ይለወጣል>> ከሚያስብል ድምዳሜ ላይ የሚያደርሰን አይሆንም። እንዲያውም እዚህ ላይ የኢትዮጵያ መንግስት ፈርጠም ያለ ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ አቅም ስላለው ኃይልን ተጠቅሞ የኤርትራ መንግስትን ለምን አይጥለውም? የሚል ጥያቄም አላነሳም። ምክንያቱም የዚህ ዓይነቱ ስልት ባሁኗ ዓለማችን ባንዲት ሉዓላዊ መንግስት ላይ ሊፈጸም የማይችል ድርጊት ስለሆነ የሚታሰብ አይደለም።

## መ. <u>ቀይ ባሕርና ጂኦ ፖለቲካው፥</u>

የቀይ ባሕር አካባቢ ከፍተኛ የዓለም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚደረግበት፥ በርካታ መርከቦች በስዊዝ ካናልና በባብኤል ማንዴብ ሸርጦች የሚተላለፉበት፥ በርካታ አገራት ትኩረት ሰጥተውት ፀጥታው የተረጋጋ እንዲሆን የሚጓጉለት፥ በርካታ ያካባቢው አገራት በባሕር መተላለፊያው ላይ ጉልህ የሆነ ተጽእኖ ሊያደርጉበት የሚፈልጉት መተላለፊያ፥ አንዳንዶቹ አገራት ደግሞ ይባስ ብሎም ያካባቢው ሁነኛ አዛዦች ለመሆን የሚፈልጉት ዓለም አቀፋዊ መተላለፊያ ነው። አንዳንዶቹ አገራት ደግሞ ባካባቢው ላይ ተጽእኖ ወይም ኃይላቸውን በማሳየት ሌሎች ተቀናቃኝ አገራትን ሊገዱቡት ይፈልጋሉ። በመሆኑም ያካባቢው አገራት በቀይ ባሕር መተላለፊያ ላይ ምንም ሳንካ እንዲፈጠር አይፈልጉም፥ ሰላማዊ ሆኖ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ተግባራትን ለማከናወን ይመኛሉ። ሆኖም በጥባጭ በተለይም አሸባሪዎች በበዙባት ዓለማችን እንደቀይ ባሕር ዓይነቱ መተላለፊያ የጥቃት ወይም የአሸባሪዎች ዒላማ ለመሆን የተመቻቸ ሊሆን ስለሚችል ጥቃቱን ለማስቀረት አገራት ባካባቢው ላይ ትኩረት ማድረጋቸው የግድ ይላል።

አሜሪካ፥ ያውሮጳ ሕብረት፥ ሩስያ፥ ቻይና፥ ጃፓን ወዘተ... በርቀት ከሚገኙ አገራት መካከል በቀይ ባሕር ላይ ከፍተኛ ትኩረት አድርገው ከሚንቀሳቀሱ አገራት ጥቂቶቹ ናቸው። ከቅርብ አገራት ደግሞ እነ ሳዑዲ አረብያ፥ ኢራን፥ ግብጽ፥ የዓረብ ኢምሬት፥ ኳታር፥ እስራኤል፥ ቱርክ፥ ወዘተ... ከፍተኛ ትኩረት የሚያደርጉበትና ፍላጎታቸውንና ኃይላቸውን የሚያሳዩበት አካባቢ ሆኗል። እንደ አሜሪካ፥ ቻይናና ያውሮጳ ሕብረት የመሳሰሉት አገራት ከባሕር ውንብድና /ፓይረሲ/ ጋር በተያያዘ በጂቡቲ ላይ ወታደራዊ ካምፕ መስርተው ከከተሙ ቆይቷል። አሜሪካ ብቻ በጦር አይሮፕላኖች፥ በድሮኖች ወዘተ...የሚደገፍና ወደ 4.500 የሚጠጋ የወታደራዊ ኃይል በጂቡቲ ካሰፈረች ከራርማለች። ቻይናም በዚህችው ትንሽ የምስራቅ አፍሪካ አገር ላይ ወታደራዊ ካምፕዋን ሰርታ ጨርሳለች። ባጠቃላይ ወደ 10.000 ወታደር የሚይዝ ካምፕ አቋቁማለች። ጃፓንም እንዲሁ ለአነስተኛ ኃይል የሚሆን ካምፕ አላት። ከ4.000 በላይ ወታደር የሚይዘው የፈረንሳይ ካምፕ ቋሚነቱ አገሪቱ ነጻ ከወጣችበት ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ የቀጠለ ነው። (7) አሁን ደግሞ ሳዑዲ አረብያ የየመን ሁቲዎችን እወጋለሁ በሚል ሰበብ በጂቡቲ ወታደራዊ ካምፕ ለመመስረት ውሏን ተፈራርማ ካምፑን ለማደራጀት እያሸበሸበች ትገኛለች።

በሌላ በኩል ደግሞ የተባበሩት የዓረብ ኤሚሬት ከኤርትራ መንግስት ጋር በፈጸመችው ወታደራዊ ውል መሰረት በዓሰብና አካባቢው ለፈጣን ወታደራዊ አውሮፕላኖች፣ ሄሊኮፕተሮች፣ ወታደራዊ ጀልባዎች ወዘተ.. የሚሆን ካምፕ በማቋቋም ላይ እንደምትገኝ ይነገራል። የግብጽ መንግስት ደግሞ በምጽዋ አካባቢ የራሱን ወታደራዊ ካምፕ ለማቋቋም እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ይነገራል።(8)

ከላይ የተጠቀሰው ሁኔታና ወታደራዊ አሰላለፍ በኢትዮጵያና ኤርትራ ላይ ለወደፊቱ ምን ዓይነት ጂኦ ፖሊቲካዊ ተጽእኖ ሊፈጥር ይችላል? ሁለቱን አገራት በመካከላቸውም ይሁን ከሌሎቹ ተዋናይ አገራት ጋር ወደ በለጠ ፍጥጫ ሊያስገባቸው የሚችል ሁኔታ ሊከሰት ይችላል ወይ? ሁለቱም መንግስታት አሁን ባላቸው ፍጥጫ ከቀጠሉ ያካባቢውን ወቅታዊ ፖሊቲካዊ አሰላለፍ አንዱ ሌላውን ለመጉዳት ሊጠቀሙበት ይችሉ ይሆን ወይ? ወዘተ... የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳቱ ተገቢ ይመስለኛል። ባሁኑ ወቅት ለጥያቄዎቹ መልስ መስጠት መሞከር ግምታዊ ከሚሆን በስተቀር በማስረጃ ላይ የተደገፈ አስተያየት ስለማይሆን ወደ ቀጣዩ ርእስ በቀጥታ ማለፍና ከርእሱ ጋር አያይዞ ስለመፍትሔ መንገዱን መሻት ግን ሊጠቅም ይችላል።

ሠ. <u>የዲፕሎማሲ ጥረት፣</u>

ዲፕሎማሲ ሲባል ሁለቱንም አገራት የሚመለከት የዲፕሎማሲ መንገድን ለመግለጽ ነው። ሁለቱም አገራት ከሌሎች መሰልና ግጭት ውስጥ ገብተው ችግራቸውን በዲፕሎማሲ ከፈቱ ወይም ለመፍታት ጥረት ካደረጉ መንግስታት ጋር አያይዞ ማስቀመጡና ማነጻጸሩ ተገቢ ይሆናል። እስካሁን ድረስ እንደታየው ሁለቱም አገራት ችግራቸውን ለመፍታት በዲፕሎማሲው መንገድ ተገቢ ጥረት አላደረጉም። ሁለቱም አገራት በሚያለያያቸው ላይ ትኩረት ከማድረግና አንዱ ሌላውን ለመጉዳት ጥረት ከማድረግ በስተቀር ቆም ብለው <<እስቲ ለዲፕሎማሲው መንገድ ወይም መፍትሔ አማራጩን እንፈልግለት>> ብለው ሲንቀሳቀሱ አልታዩም። ብዙውን ጊዜ እንዳየነው አንዱ አገር ሌላውን ለመጉዳት የሆነ እርምጃ ወይም እንቅስቃሴ ሲያደርግ ሌላኛው አገር ደግሞ <<በል እንገዲህ የኔ ምትና አጸፋ ደግሞ ምን እንደሚመስል ቅመሰው>> የሚል ዓይነት ግብረ መልስ ሲሰጣጡ እንጂ በሰለጠነ መንገድ ወይም በዲፕሎማሲያዊ መንገድ <<እኔ ይህንን አድርጊልሃለሁ፣ ካንተ ደግሞ አዎንታዊ ግብረ መልስ እጠብቃለሁ፣ እኔ አንተን ለመርዳት ይህንን እርምጃ ወስጃለሁ፣ አንተ ደግሞ የኔን ቀና አመለካከትና እርምጃ ከግምት ውስጥ አስገብተህ ምን ለማድረግ እንደምትፈልግ አያለሁ፣ ወዘተ...>> የሚመስል ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ አልታዩም። ካለፉት ዓመታት አካሄዳቸው እንደምንገነዘበው ሁለቱም አገራት ለዲፕሎማሲው ሂደትና መፍትሄ ትኩረት አድርገው ሲንቀሳቀሱ አልታዩም። ከሁለቱም አገራት እርምጃ የምናየው ነገር አንዱ በሌላኛው ላይ ምን ያህል ጎል እንዳስገባና <<ጉድ አደረግኩት፣ ሰራሁለት! ወዘተ...>> የሚመስል እንቅስቃሴ ሲያሳዩ ነው የከረሙት። ይህ ድርጊት ደግሞ የሌሎች ጎረቤት አገራት መሳቂያና መሳለቅያ ከመሆን በስተቀር ለአገራቱ ሰላምና የወደፊት የጋራ እድገት የሚበጅ አይደለም። በርግጥ ነው የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራዊያን ስደተኞችን በመቀበልና በተለያየ ዘርፍ በመርዳት ያደረገው አስተዋጽኦ ከላይ የጠቀስነው ጉዳይ ስለሆነ እዚህ ላይ መድገሙ ተገቢ አይሆንም። ነገር ግን በሁለቱም ኢምባሲዎች አካባቢ የጋራ ግንኙነትን በግልጽም በምስጢርም በመፍጠር ለዲፕሎማሲው እንቅስቃሴ የሚበጁ ተግባራት ሲከናወኑ አልታዩም። የሁለቱም አገራት ዲያስፖራን ዒላማ በማድረግ ለዲፕሎማሲው ግንኙነት ሊረዱ የሚችሉ ግልጽም ምስጢራዊም እንቅስቃሴዎች ሲካሄዱ አልታዩም። ስደተኞችን ዒላማ በማድረግ ከአገር ቤት ዘመዶቻቸውና ጓደኞቻቸው ጋር ግንኙነቶችን በመፍጠር የዲፕሎማሲውን ምሕዳር ለመጠቀም የሚረዱ ተግባራት ሲከናወኑ አልታዩም። የሁለቱንም አገራት ምሁራን /በተለይም

ከውጭ የሚገኙትን/ መሰረት በማድረግ በሁለቱም አገራት የወደፊት ግንኙነት አስመልክቶ ምን ማድረግ እንደሚበጅ የሚያመላክቱ እንቅስቃሴዎች በስፋት ሲካሄዱ አልታዩም፣ ወዘተ... በዚህ ሂደት የተወሰነ እርምጃ ቢከድበት ኖሮ በርካታ ጠቃሚ ውጤቶች ወይም አዎንታዊና ጠቃሚ መንገዶች ይታዩ ነበር። ይህ ባለመደረጉ ሂደቱ የጠፋ ጊዜ ነበር ከማለት ውጭ በሌላ ሁኔታ መፈረጅ የሚቻል አይመስለኝም።

በዚህ ርእስ ላይ እየተነጋገርን የምንገኘው የዲፕሎማሲውን ምሕዳር ሁለቱም አገራት ምን ያህል ተጠቅመውበታል? ምን ያህል ምሕዳሩን በመጠቀም ሰላማዊ መፍትሄ ለማምጣት ሞክሯል? ተነሳሽነቱን በመውሰድ የዲፕሎማሲውን ምሕዳር በጥንቃቄና በብልጠት ለመጠቀም ዋናውን ሚና መጫወት የነበረበት የትኛው አገር ነው? አንዱ አገር ተነሳሽነቱን ሲወስድ ሌላኛው አገርስ ምን ማድረግ ይጠበቅበት ነበር? ወዘተ... የመሳሰሉ ጉዳዮችን አንስተን ለመወያየት የሚረዳ ይመስለኛል።

1. በመሰረቱ ኤርትራ በኢትዮጵያ ውስጥ ህውከትና ብጥብጥ እንዲፈጠር ከፍተኛ ጥረት ስታደርግ መቆየቷ አሌ የማይባልና የታወቀ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ኤርትራ በምስራቅ አፍሪካ ካሉት አገራት ከጂቡቲ ቀጥላ ትንሽዋ አገር ናት። የሕዝቧ ብዛትም ቢሆን ከአምስት ወይም ስድስት ሚልዮን የሚበልጥ አይደለም። ነገር ግን የኤርትራ መንግስት ከእግሩ መጠን በላይ ጫማ ለማድረግ እንደሚሞክርም ይታወቃል። ባንጻሩ ደግሞ ኢትዮጵያ ባካባቢው ትልቅ አገር ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ ሕብረት መቀመጫና በዓለም ውስጥ ከኒው ዮርክና ከለንደን ቀጥሎ ከፍተኛ የዲፕሎማቲክ ጽ/ቤቶች ያሏት አገር ናት። ኢትዮጵያ የጎረቤቶቿን አገራት ማለትም የኬንያ፣ የሱዳን፣ የደቡብ ሱዳን፣ የሶማሊያ፣ የኤርትራና የጂቡቲ ሕዝብ ባጠቃላይ ተደምሮ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በቁጥሩ ያንሳል። ባሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ወደ 102 ሚልዮን አካባቢ ደርሷል። ይህም የሚያሳየው ኢትዮጵያን ከኤርትራ ጋር በተለያዩ ንጽጽሮች ማወዳደሩ ተገቢ አይሆንም ለማለት ነው።
2. እንደሚታወቀው ሁለቱም አገራት በተለያዩ ዘዴዎች ማለትም በፖለቲካው፣ በዲፕሎማሲው፣ በኢኮኖሚው፣ በማሕበራዊው፣ በወታደራዊና በኢንተሊጀንሳዊ ተግባራት ሲጠቃቁ ከርሟል። በርግጥ አንዱ በሌላኛው ላይ የበለጠ ጉዳት አድርሶበታል በማለት ዝርዝሮችን ማቅረብ ይቻል ይሆናል። ነገር ግን ላሁኑ ጉዳያችን የሚጠቅም አይደለም። ጉዳት መድረሱ ብቻ መጥቀሱ በቂ ነው። ይህ ጉዳት እንዲቀርና ሁለቱም አገራት ወደ መደበኛው የዲፕሎማሲ ግንኙነት ገብተው ሰላማዊ ሁኔታ እንዲፈጥሩ ምን መደረግ አለበት? ወደሚለው ማተኮሩ ነው ሊበጅ የሚችለው።
3. ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ኤርትራ ትንሽ አገር በመሆኗና ኢትዮጵያ ደግሞ በተነጻጻሪ ትልቅ አገር በመሆኗ በሁለቱም አገራት መካከል በሚካሄድ መጠቃቃት በሌሎች ታዛቢ ወይም ተመልካች አገራት ዘንድ የሚታዘንላት አገር ማን ትሆናለች? ተብሎ ቢጠየቅ ኢትዮጵያ ናት የሚል መልስ ከየትም አቅጣጫ ማግኘት እንደሚከብድ የታወቀ ነው። ለምን ቢባል ኤርትራ አሁንም ትንሽ አገር በመሆኗ ከፍተኛ ጥፋት የተፈጸመው በርሷ መሆኑ ከበድ ያለ ማስረጃ ይቅረብ ብለን ብንገምትም ኤርትራ ናት አጥቂዋ ብሎ የሚቀበል አገር ብዙም አይኖርም። <<እንዴት ትንሽ አገር ትልቅ አገርን ለመጉዳት ትችላለች?>> የሚል ጥያቄ በማንሳት ነው ኢትዮጵያን አጥቂ አድርጎ ለማስቀመጥ የሚሞከረው። ለምሳሌ ባውሮፓ በተለይም የስካንዴነቪያን አገራትና የአውሮጳ ሕብረት አባል አገራት በሙሉ (ከጥቂቶቹ በስተቀር)፣ እነጣሊያን፣ እነስሎቬንያ፣ ክሮኤሽያ፣ ሞንተነግሮ፣ መቆደንያ፣ ወዘተ... የመሳሰሉት አገራት የኤርትራ ነባር ደጋፊዎች ሆነው የኖሩና አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያን አጥቂ

አድርገው ከመፈረጅ የማይመለሱ አገራት ናቸው። ለምን ቢባል ይህ ሁኔታ በተለይም የስካንዴነቪያን አገራትን ብንወስድ ከትጥቅ ትግሉ ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የዘለቀና አንዳንዶቹም ትናንሽ አገራት በመሆናቸው ኤርትራን አጥቂ አድርገው ለመውሰድ የሚቸገሩ ናቸው። በአረቡ ዓለምና በሌሎችም አህጉር የሚገኙ ትናንሽ አገራትም ቢሆኑ ከላይ ከተጠቀሰው አቋም የተለየ አቋም ለመያዝ ይከብዳቸዋል። በነገራችን ላይ ኤርትራ የአረብ ሊግ ታዛቢ አባል አገር መሆኗንም መዘንጋት የለበትም። ለማንኛውም እዚህ ላይ ደጋፊና ተቃዋሚ አገር በመፈረጅ ለጉዳዩ ውጤታማነት ተገቢነት ይኖረዋል ለማለት ሳይሆን ኢትዮጵያ ትልቅ አገር በመሆኗ <<በኤርትራ ተጠቃች>> የሚለውን አባባል ለምን ተቀባይነት ሊያጣ እንደሚችል ለመጠቋቆም ብቻ ነው።

4. በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ስለመሆኗና በዓለም መድረክ ተሰሚነቷ እየተጠናከረ በመምጣቱ ምክንያት በተባበሩት መንግስታት ለፀጥታው ምክር ቤት ተለዋጭ አባልነት ከ190 ተሳታፊ አገራት የ185 ድጋፍ አግኝታ ከጀንዋሪ 01/2017 ጀምሮ ወንበሯን ለመያዝ ችላለች። ድጋፍ የነፈጉዋት አምስቱ አገራት ኤርትራ፣ ግብጽ፣ ሳዑዲ አረብያ፣ ኳታርና ሴኔጋል ብቻ ነበሩ። እያንዳንዱ አገር የየራሱ ምክንያት ይኖረዋል። ስለሆነም ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ ከኤርትራ ጋር በትንሹም በትልቁም ጉዳይ እንካ ስላንቲያ እየገባች ለመቀጠል መሞከር ያለባት አይመስለኝም። ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር እየተነታረከች መኖሯ አይምርላትም፣ አይበጃትምም። ለኢትዮጵያም የተባበሩት መንግስታቱ መድረክ ከኃያላኑ አገራትና ከመሰል አባል አገራት ጋር በቀላሉ የሚያገናኛት በመሆኑ መድረኩን ከኤርትራ ጋር ላላት የሻከረ ግንኙነት ለመለወጥ የምትጠቀምበት መሆን ይኖርበታል ባይ ነኝ። ስለሆነም ለዲፕሎማቲክ ግንኝነቱ ተነሳሽነቱን ወስዳ መንቀሳቀስ የሚኖርባት አገር ኢትዮጵያ ናት።

5. አንዱና በቅድሚያ ኢትዮጵያ ልትገነዘበው የሚገባው ጉዳይ የኤርትራ መንግስት ባንድ ወቅት በራሱ መንገድ ይወድቃል ብላ ከመጠበቅ ይልቅ አሁን በስልጣን ላይ ካለው የኤርትራ መንግስት ጋር በጉርብትና በሰላም ለመኖር የዲፕሎማሲ ጥረቷን መቀጠል ያለባት ይመስለኛል። ኢትዮጵያ ከምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታት ጀምራ ኤርትራ ወደ ክፍለ አህጉሩ ድርጅት እንድትመለስ የራሷንና የአባላቱን ተሳትፎ ተጠቅማ እንቅስቃሴ ብታደርግ በኤርትራ መንግስት ዘንድ ጥሩ የዲፕሎማቲክ እይታ /ዲፕሎማቲክ ጀስቸር/ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ይህንን እርምጃ መውሰድ የኢትዮጵያን ታላቅነት የሚያሳይ እንጂ የኢትዮጵያን ክብርና ሞገስ የሚቀንስ አይሆንም። ይህ በበይነ መንግስታቱ ደረጃ የሚወሰድ እርምጃ የኤርትራ መንግስትን ባህርይ ሊለውጥ የሚችል ብሎም ደረጃ በደረጃ በተባበሩት መንግስታት ዘንድ የተጣለበትን ማእቀብ ለማንሳት ስለሚረዳው ጠቃሚነቱና ለወደፊቱ ሊከፈት የሚችለውን የጋራ ግንኙነት ወይም በሦስተኛ ወገኖች እገዛ ሊመጣ የሚችልን የዲፕሎማቲክ ግንኙነትን እያጠናከረ ሊሄድ ይችላል። ተነሳሽነቱ ግን አሁንም በኢትዮጵያ መንግስት ዘንድ መወሰድ ይኖርበታል እላለሁ።

6. ኢትዮጵያ አሁንም ሌላ ተጨማሪ አዎንታዊ የዲፕሎማቲክ ጀስቸር እርምጃዎችን ለመውሰድ ዝግጁ መሆንዋንና ይህም የሚወሰነው የኤርትራ መንግስት በሚወስደው እርምጃና በሚያሳየው አዎንታዊ ግብረ መልስ እየተመዘነ እንደሚሆን በይፋ መግለጽ መቻል ይኖርበታል እላለሁ። ለምሳሌ የኤርትራ መንግስትን ለማጥቃት ፍላጎት ወይም እቅድ እንደሌላት፣ ይልቁንም አዎንታዊ ግንኙነቱ እየተሻሻለ የሚሄድ ከሆነ <<ኢትዮጵያ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የኤርትራ ወደቦችን ለመጠቀም እንደምትፈልግ፣ የሕዝብ ለሕዝብና የመንግስት ለመንግስት ግንኙነቱን ለማሻሻል እንደምትፈልግ፣ ኢትዮጵያ ለኤርትራ መንግስትም ቢሆን የኤሌክትሪክ ኃይልን ለመሸጥ እንደምትፈልግ ወዘተ…>> የመሳሰሉ እቅዶችን በይፋ መግለጽ ትችላለች።

እንዲህ ዓይነቱ መግለጫ የኤርትራ መንግስት ካንጼም ሁለቴ ሊያስብበትና አዎንታዊ መልስ ሊሰጥበት ይችላል።

7. በኤርትራ መንግስት በኩል ደግሞ በተግባር ላይ ሊውል የማይችለውን <<የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ አሁኑኑ ይተግበርልኝ>> የሚለውን ጥያቄ ለጊዜው ቢተወውና ከላይ በጠቀስኩዋቸው ጉዳዮች ላይ በማተኮር ግንኙነቱን ለማሻሻል ቢንቀሳቀስ ይጠቅማል እላለሁ። የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ በቀጣዩ ጊዜ ሊታይ ይችላል። አሁን ግን የድንበር ኮሚሽኑ ጉዳይ ላጠቃላይ ግንኙነቱ ደንቃራ ሆኖ እንዲቀጥል የኤርትራ መንግስት መፍቀድ ያለበት አይመስለኝም።

ውድ አንባቢያን ይህ ከላይ ያቀረብኩት አስተያየት ለመጻፍ የተገደድኩት በጉዳዩ ላይ በርካታ ፀሐፊዎች ከዚህ የተሻለ ሐሳብ ሊኖራቸው እንደሚችልም በመገመት ነው። ሆኖም ይህ ፅሑፍ እንዳንድ መነጋገሪያ ጉዳይ ሊወሰድ ከቻለ በቂ ነው። ጉዳዩ ይመለከተናል የምንል ወገኖች በርእሱ አጥብቀንና በዝርዝር ልንነጋገርበት ይገባል ባይ ነኝ። የሁለቱም አገራት ፍጥጫና ቅራኔ ለቀጣዩ ትውልድ መተላለፍ ያለበት አይመስለኝም። ችግሩን የፈጠረው ይህ ትውልድ ስለሆነ መፍትሔውንም ማምጣት ያለበት ይህ ትውልድ ነው። ቀጣዩ ትውልድ ይህ ትውልድ ለፈጠረው ችግር ወራሽ የመሆን ግዴታ የለበትም።

አመሰግናለሁ!

ገራገር ዘበርጋ

---

**ዋቢዎች፥**

(1) ስማቸውን መጥቀሱ አስፈላጊ ያልሆነና ከዚህ በፊት በዘላምበሳ አካባቢ መኖሪያቸው ከሆኑ ግለሰቦች ያገኘሁት መረጃ።

(2) ስማቸውን መጥቀስ አስፈላጊ ባለመሆኑ ያልጠቀስኩዋቸው ሰዎች የሰጡኝ መረጃ። (በነገራችን ላይ የዚህ ዓይነቱ መረጃ በትግራይ ወይም አፋር አካባቢ ለሚኖር ሰው እንደ አዲስ ነገር ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም። ምክንያቱም የተለመደ ነው። አንዳንዴም ጉዳዩ ከኮንትሮባንድ ጋር ይያያዛል።)

(3) ባዲስ አበባ ኮንደሚንየም ቤቶች በርካታ ወጣት ኤርትራዊያን ተሰባበው እንዲኖሩ የተገደዱበት ምክንያት ቤቶቹ ባንድ ቦታ ላይ ሰብሰብ ብለው ስለሚገኙ፥ ማሕበራዊ ሕይወታቸውን ሰብሰብ ብለው ለማሳለፍ ስለሚመቹና በቅርብ ለመገናኘት ስለሚያስችሉ ይመስለኛል። በመሆኑም በሺዎች የሚቆጠሩ ኤርትራዊያን ወጣቶች አሰልቺና ገደብ የሌለው ሕይወት ስራ ፈትተው ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ ይታያሉ። (ፀሐፊ በቅርበት በዓይኔ ያየሁት ክስተት ነው።)

(4) ስሙን ከማልጠቅሰው ካንድ ታማኝ የቅርብ ሰው ያገኘሁት መረጃ ነው።

(5) Stephanie Goche, Future Directions International. *Djibouti: A Tiny Haven with Strategic Importance in a troubled Neighbourhood.* Ed. December 1/2016.

(6) Ibid.

(7) Shaqsy.com, *Djibouti Finalising Deal for Saudi Military Base.* January 18/2017.

(8) Ibid.